# አቤቱታ የማቅረብ መብት እና ያለአግባብ የተደረገ እስራትን አስመልክቶ ከኢሰመጉ የተሰጠ መግለጫ

ህዳር 29/2015 ዓ.ም

## መግቢያ፡

በኦሮሚያ ክልል ወለጋ ዞን በተለያዩ አካባቢዎች በሚገኙ ነዋሪዎች ላይ ከፍተኛ ጥቃት እየደረሰ እና የህይወት ዋጋ እያስከፈለ መሆኑን በመግለጽ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ(ኢሰመጉ) ለሚመለከተው አካል እንዲያሳውቅልን ሲሉ 28 ሰዎች በ24/03/2015ዓ.ም ልደታ በሚገኘው የኢሰመጉ ማዕከላዊ ቀጣና ጽ/ቤት በመገኘት ያመለከቱ ሲሆን አቤቱታውን አቅርበው ከጽ/ቤቱ እንደወጡ ከ28 ሰዎች መካከል 22 ሰዎችን ፖሊስ ይዞ ተክለሃይማኖት አካባቢ በሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ ከ24/3/2015 ዓ.ም ጀምሮ ያሰራቸው ሲሆን የኢሰመጉ ባለሞያዎች ግለሰቦቹ ከታሰሩበት ዕለት አንስቶ የት እንዳሉና ያሉበትን ሁኔታ በማጣራት የሚመለከታቸውን ኃላፊዎች አነጋግረው ያገኙት መረጃ ሰዎቹ የታሰሩት ለፖሲስ በደረሰው ከጸጥታ ጋር የተያያዘ የተጋነነ መረጃ እንደሆነ ነው፡፡

በተደረገው ውይይት በአስቸኳይ ሊፈቱ እንደሚችሉ በተገባልን ቃል መሰረት በ27/3/2015 ዓ.ም አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አራዳ ምድብ ችሎት ቀርበው እያንዳንዳቸው በገንዘብ ዋስ እንዲወጡ ተደርጓል፡፡

ሆኖም የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ) ለአቤቱታ የሚመጡ አካላት በነጻነት ያለምንም መሸማቀቅ አቤቱታቸውን ሊያቀርቡ የሚገባበት በህግ አግባብ የተቋቋመ ነጻ ድርጅት መሆኑ እየታወቀ ከላይ የተጠቀሱት 28 አቤቱታ አቅራቢዎች ጉዳዮቻቸውን ይዘው ወደ ድርጅታችን መምጣታቸውን ተከትሎ ከመካከላቸው 22 ሰዎች ለእስር መዳረጋቸው ተገቢ እንዳልነበረ ኢሰመጉ ያምናል፡፡ ይህ ከህግ አግባብ ውጭ የሆነ ድርጊት አቤቱታ አቅራቢዎች የደህንነት ስጋት እንዲያድርባቸው የሚያደርግ በመሆኑ በዚህ ወቅት እንዲህ አይነት ሁኔታ መታየቱ አግባብነት የሌለውና በህግ የሚያስጠይቅ በመሆኑ ከዚህ በኋላ ተመሳሳይ ድርጊት እንዳይፈፀም ኢሰመጉ ማሳሰብ ይወዳል።

## ተያያዥ የህግ ድንጋጌዎች፡

የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 30(1) ላይ በግልጽ ተደንግጎ እንደሚገኘው ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሳሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣አቤቱታ የማቅረብ መብት እንዳለው

ይደነግጋል፡፡ በሌላ በኩል የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል-ኪዳንም(ICCPR) አንቀጽ 9 ማንኛውም ሰው የሰውን ነፃነትና ደህንነት የማግኘት መብት አለው። ማንም ሰው በዘፈቀደ ሊታሰር እንደማይችልና ማንም ሰው በህግ በተደነገገው መሰረት ካልሆነ በቀር ነፃነቱን እንደማይገፈፍ በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ በተመሳሳይ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ(UDHR) አንቀጽ9 ላይ ማንም ሰው በህግ በተደነገገው መሰረት ካልሆነ በቀር ነፃነቱን እንደማይገፈፍና በዘፈቀደ ሊታሰር እንደማይገባ በግልጽ አስቀምጧል፡፡

## የኢሰመጉ ጥሪ፡

- በኦሮሚያ ክልል ወለጋ ዞን በተለያዩ አካባቢዎች በሚገኙ ነዋሪዎች ላይ ከፍተኛ ጥቃት እየደረሰ እና የህይወት ዋጋ እያስከፈለ መሆኑን በአካል በመምጣት የገለጹ 22 የሚያህሉ ሰዎችን ፖሊስ ደረሰኝ ባለው ከጸጥታ ጋር የተያያዘ የተጋነነ መረጃ አስሮ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ምንም እንኳን ከቀናት አስር በኋላ በዋስ እንዲወጡ ቢደረግም ይህ ድርጊት የዜጎችን ያለአግባብ ያለመታሰር መብትና አቤቱታ የማቅረብ መብት ሰዎችን የመንቀሳቀስ መብቶችን አላግባብ የሚገድብ የፀጥታ አካላት ስልጣንን አላግባብ የመጠቀም ድርጊት በመሆኑ እንደዚህ አይነት ድርጊት በድጋሚ እንዳይፈጸም ኢሰመጉ ያሳስባል፤
- ይህ ድርጊት በመፈጸሙ ሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎችም አቤቱታቸውን ለኢሰመጉ ወይም ለሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት ለመግለጽ እንዲፈሩና በሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ላይ እምነት እንዳይኖራቸው የሚያደርግ ድርጊት በመሆኑ የፀጥታ አካላት ከእንዲህ አይነት ድርጊት እንዲቆጠቡ ኢሰመጉ ያሳስባል፤
- የሃገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ የማህበረሰብ አንቂዎች ፣ሚዲያዎች፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና የሚመለከታቸው የማህበረሰብ ክፍሎች በሙሉ በአካባቢው በሚኖሩ ያልታጠቁ የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ እየደረሰ ያለውን አስከፊ ጥቃቶች ለማስቆም እንዲሁም በአቤቱታ አቅራቢዎች ላይ የሚደርሱ የመብት ጥሰቶችን ለመከላከል የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

አዲስ አበባ ፣ኢትዮጵያ